
# ★★ EVERY KID IN A PARK




## ለ4ኛ ክፍል ተማሪዎችና ለእንግዶቻቸው የፌዴራል መሬትና ውሃ አገልግሎት ነጻ ተደራሽነት

Amharic

## እያንዳንዱ ሕጻን በትምህርት፣ በአዲስ ነገር ግኝነትና በሳቅ የተሞላ ዓለም ይጠብቀዋል!

ለሁሉም የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበ ጥሪ! ስለ አሜሪካ የፌዴራል መሬትና ውሃ ምን ያውቃሉ? ሁሉም ቦታ ሊባል በሚችል ሁኔታ ሊያገኟቸው ይችላሉ! ከፖርቶ ሪኮ እስከ ሜይን እና ከቨርጂኒያ እስከ ፓስፊክ ደሴቶች ድረስ፣ አሜሪካ ካሏት በጣም ድንቅ መዳረሻ ቦታዎች መካከል የተወሰኑት የእርስዎን ጉብኝት ይጠባበቃሉ፡፡
ስለ ማንነት ቅርስዎ አውቀው ከተፈጥሮ ጋር በመገናኘት ከ400 በላይ ብሔራዊ ፓርኮችና በሚሊዮን ሔክታር የሚቆጠር የፌዴራል መንግስት መሬትና ውሃን ያስሱ፡፡ በሐይቆች መካከል ያለ መሬት፣ ቻናል አይላንድስ፣ ሴንት ሉዊስ አርክ፣ ሳን አንቶኒዮ ሚሽንስ፣ ዘ ፍሬደሪክ ዳግላስ ሆም፣ ካንዮን ኦፍ ዘ አንሼንትስ እና ዘ ፍሎሪዳ ኪይስ የተባሉ አስደሳች ቦታዎችን ይጎብኙ፡፡ የተኩላዎችን ጩኸት ያድምጡ፣ የቅድመ ታሪክ የዳይኖሰር ዳናዎችን ይመልከቱ፣ ወንዝ ያቋርጡ፣ በልዊስና ክላርክ ዱካ ላይ ይራመዱ ወይም የደመቀ ምሽት ሰማይን ቀና ብለው እያዩ ከዋክብትን ይፈልጉ!

*ማለፊያ ትኬትዎን እንዴት ማግኘትና መጠቀም እንዳለብዎ ተጨማሪ መረጃ ለማየት፣ ጉዞዎትን ሊያቅዱ ገጽ ለማግኘት፣ ተገቢ የሆኑ የትምህርት ቁሳቁሶችን ለማግኘት፣ ልዩ ፕሮግራሞችና አድራሻዎችን ለማግኘት ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ www.everykidinapark.gov*

**www.everykidinapark.gov**

## ሁሉም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ተጋብዘዋል፡፡

Every Kid in a Park *በሚለው ፕሮግራም ውስጥ* በመሳተፍዎ፣ የፌዴራል መንግስት መሬትና ውሃን አሁኑኑ መጎብኘትና መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ለታሪክና ባህል እምቅ ፍላጎትን በማቀጣጠል ወሳኝነት ያላቸውን ቦታዎች ለማዳን የዕድሜ ልክ ቁርጠኝነትን ያነሳሱ፡፡ ስለመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባራት አጋጣሚዎች ወይም እነዚህን ልዩ ቦታዎች በመጠበቅ ረገድ ተሳታፊ ስለሚሆኑበት መንገድ ይወቁ፡፡

ከሴፕቴምበር 1,2015 ጀምሮ፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ የ4ኛ ክፍል ተማሪ (ቤት ውስጥ የተማሩና ዕድሜያቸው 10 ዓመት የሞላቸው የነጻ ምርጫ ተማሪዎችን ጨምሮ) ከሆኑ፣ ለአንድ ዓመት ያህል ወደማንኛውም የፌዴራል መንግስት መሬት ወይም ውሃ ያልተገደበና ነጻ ተደራሽነት እንደኒርዎ የሚያስችልዎን የራስዎን ቫውቸር ዳውንሎድ ማድረግ (ማውረድ) ይችላሉ!

## ማለፊያ ትኬትዎን ይውሰዱ!

ማለፊያ ትኬት ማግኘት ቀላል ነው! www.everykidinapark.gov የሚለውን ድረ ገጽ "Get Your Pass"የሚል ክፍል በመጎብኘት የኦንላይን ጨዋታ ማጠናቀቅና ግለሰባዊ የሆነ ቫውቸር ዳውንሎድና ፕሪንት አድርገው የፌዴራል መንግስት መሬትና ውሃ በሚገኙባቸው ቦታዎች ላይ መጠቀም ይችላሉ፡፡ ይህን የወረቀት ቫውቸር ቶሎ በማይጎዳ፣ የኢንተር ኤጀንሲ ዓመታዊ የ4ኛ ክፍል ማለፊያ ትኬት በተወሰኑ የፌዴራል መንግስት መሬቶችና ውሃ ቦታዎች ላይ መቀየር ይቻላል፡፡ ማለፊያ ቲኬቶች የሚሰጡባቸውን ቦታዎች ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት ድረ ገጹን ይጎብኙ https://store.usgs.gov/pass/PassIssuanceList.pdf

የማለፊያ ትኬት ተቀባይነትና የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎ፣ እባክዎ በቀጥታ ለፌዴራል መንግስት የመሬት ወይም ውሃ ክፍል ያሳውቁ፡

- Bureau of Land Management (ቢሮ ኦፍ ላንድ ማኔጅመንት) (www.blm.gov)
- Bureau of Reclamation (ቢሮ ኦፍ ሬክላሜሽን) (www.usbr.gov)
- U.S. Fish and Wildlife Service (ዩኤስ ፊሽ ኤንድ ዋይልድ ላይፍ ሰርቪስ) (www.fws.gov)
- National Oceanic and Atmospheric Administration (ናሽናል ኦሽኒክ ኤንድ አትሞስፌሪክ አድሚኒስትሬሽን) (www.oceanservice.noaa.gov)
- National Park Service (ናሽናል ፓርክ ሰርቪስ) (www.nps.gov)
- U.S. Army Corps of Engineers (ዩኤስ አርሚ ኮርፕስ ኦፍ ኢንጂነርስ) (www.corpslakes.us)
- U.S. Forest Service (ዩኤስ ፎረስት ሰርቪስ) (www.fs.fed.us)







## በቫውቸር ወይም በማለፊያ ትኬቱ ውስጥ የተካተተ ማነው?

ቫውቸር ወይም ማለፊያ ትኬት የያዘ የ4ኛ ክፍል ተማሪ በመሆንዎ፣ እርስዎ ባሉበት ተሽከርካሪ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ሰው በመኪና በሚያስከፍሉ ቦታዎች ላይ ከክፍያ ነጻ እንዲገባ ይፈቀድለታል፡፡ የሚጎበኙት ቦታ በሰው ልክ የሚያስከፍል ከሆነ፣ እስከ ሶስት የሚደርሱ አጃቢ ጎልማሶች የማለፊያ ትኬት የያዘ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ጋር ከክፍያ ነጻ መግባት ይችላሉ፡፡ የ4ኛ ክፍል ተማሪውና ቤተሰቡ ብስክሌት የሚጋልቡ ከሆነ፣ ቁጥራቸው ሶስት የሚደርስ አጃቢ አዋቂዎችም ይካተታሉ! የ4ኛ ክፍል ተማሪው የማለፊያ ትኬቱን ለመጠቀም በአካል መገኘት አለበት፡፡

አስተማሪዎችም መሳተፍ ይችላሉ! ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ዛሬውኑ ወደዚህ ድረ ገጽ ይግቡwww.everykidinapark.gov

National Park Service • Forest Service
Army Corps of Engineers • Bureau of Land Management Fish and Wildlife Service • Bureau of Reclamation
National Oceanic and Atmospheric Administration

## ከክፍያ ነጻ መግቢያ ያግኙ!

ሰራተኛ ባልተሟላባቸው አንዳንድ የፌዴራል መንግስት መሬቶችና ውሃዎች ላይ የጸና ማለፊያ ትኬት በተሽከርካሪ ውስጥ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ የኢንተር ኤጀንሲ ዓመታዊ የ4ኛ ክፍል ማለፊያ ትኬትን በመስኮት በኩል ባለው የኋላ ትዕይንት ማሳያ (ስፖኪዮ) አቅጣጫ በተንጠልጣይ ታግ ወይም በዳሽቦርድ ላይ ማሳየት ያስፈልጋል፡፡ የ4ኛ ክፍል ተማሪ ሆነው የወረቀት ቫውቸር ከያዙ፣ ቫውቸሩን ባር ኮዱ በሚታይበት አቅጣጫ ዳሽቦርድ ላይ መቀመጥ አለበት፡፡

የጉዞ ዕቅድ አወጣጥ መሳሪያዎችን ከእነዚህ ድረ ገጾች ማግኘት ይቻላል፡

- www.everykidinapark.gov
- www.findyourpark.com
- www.discovertheforest.org
- www.recreation.gov

**ስለ Every Kid in a Park ተጨማሪ መረጃ ያግኙ**

የ Every Kid in a Park ድረ ገጽ ቫውቸርና ማለፊያ ትኬት እንዴት መገኘት እንደሚችል የሚገልጽ መረጃ፣ ጉዞ ለማቀድ የሚያስፈልጉ ፍንጮችና እንዴት መሳተፍ እንደሚቻል መረጃ ይሰጣል፡፡ እባክዎ ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ www.everykidinapark.gov ወይም EveryKidinaPark የሚለውን በ Facebook, Instagram, Twitter, እና YouTube በመከታል ተጨማሪ መረጃ ያግኙ፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ www.everykidinapark.gov
እንደዚሁም በቀጣይ አድራሻችን በትዊተር ይከተሉን፡

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

**ጥ፡ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚገኙ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች (ቤት ውስጥ የተማሩና ዕድሜያቸው 10 ዓመት የሞላቸው የነጻ ምርጫ ተማሪዎችን ጨምሮ) ቫውቸር ወይም የማለፊያ ትኬት እንዴት ማግኘት ይችላሉ?**
**መ፡** ቀጣዩን ድረ ገጽ በመጎብኘት www.everykidinapark.gov ፤ የኦንላይን ጨዋታ መጫወትና ግለሰባዊ የሆነ ቫውቸር ዳውንሎድና ፕሪንት በማድረግ፡፡

**ጥ፡ ቫውቸር ወይም የማለፊያ ትኬት የሚያገለግለው ለምንድን ነው?**
**መ፡** የማለፊያ ትኬቱ ከክፍያ ነጻ ሲሆን ከሴፕቴምበር 1 እስከ ኦገስት 31 ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች በሁሉም የፌዴራል መንግስት መሬቶችና ውሃዎች ላይ የመግቢያ ክፍያና የተለመዱ የአገልግሎት ክፍያዎችን የሚሸፍን ነው፡፡ የካምፒንግ፣ የጀልባ ጉዞ፣ የፓርኪንግ፣ ልዩ ጉብኝቶች፣ የአስተርጓሚ አገልግሎት ክፍያ፣ ፈቃዶች ወይም የጀልባ ቀዘፋ የመሳሰሉ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ክፍያ አይጨምርም፡፡ በተጨማሪም፣ የግል ባለሃብቶች በፌዴራል መንግስት መሬቶችና ውሃዎች ላይ ያሉ አንዳንድ አገልግሎት መስጫ ተቋማትን የሚያስተዳድሩ በመሆኑ የማለፊያ ትኬቱን ላይቀበሉ ይችላሉ፡፡ የማለፊያ ትኬትን ተቀባይነት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃን ከሚጎበኙት ቦታ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

**ጥያቄ፡ በአንድ ቫውቸር ወይም ማለፊያ ትኬት ከአንድ በላይ ተሽከርካሪ እንዲገባ ይፈቀዳል?**
**መልስ፡** አይፈቀድም፡፡ የማለፊያ ትኬቱን የያዘ ሰው የተሳፈረበት ተሽከርካሪ ብቻ በነጻ እንዲገባ ይፈቀድለታል፡፡

**ጥ፡ ብስክሌት የሚጋልብ የማለፊያ ትኬት የያዘ ሰው በብስክሌት አብረውት የሚጋልቡ ጓደኞቹ ወደ ፌዴራል መንግስት መሬት ወይም የውሃ ቦታ እንዲገቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል?**
**መ፡** አዎ፡፡ የማለፊያ ትኬቱን የያዘውና እስከ ሶስት የሚደርሱ አብረውት የመጡ አዋቂ ብስክሌት ጋላቢዎች በነጻ እንዲገቡ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

**ጥ፡ በጠፋ ወይም በተሰረቀ ቫውቸር ወይም ማለፊያ ትኬት ምትክ ማግኘት ይቻላል? መለያ ቁጥሮችን መከታተል ይቻላል?**
**መ፡** አይቻልም፡፡ የግል መብትና የሎጂስቲክ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ለጠፋ ወይም ለተሰረቀ የማለፊያ ትኬት ምትክ አይሰጥም፤ አዲስ ቫውቸር ወይም ማለፊያ ትኬት ለማግኘት ወደ ቀጣዩ ድረ ገጽ በመግባት አዲስ የወረቀት ቫውቸር ለማግኘት የሚከናወኑ ተመሳሳይ ተግባራትን መፈጸም ያስፈልጋል፡ www.everykidinapark.gov

**ጥ፡ ቫውቸሬን ወይም የማለፊያ ትኬቴን ረስቼ ወደቦታው በመሄዴ የመግቢያ ወይም የመጠቀሚያ ክፍያ ብከፍል፣ ደረሰኙንና የማለፊያ ትኬቱን ወይም ቫውቸሩን ኮፒ በመላክ ገንዘቤን ማስመለስ እችላለሁ?**
**መ፡** ገንዘብ ተመላሽ አይደረግም፡፡ የማለፊያ ትኬት ወይም የቫውቸር ኮፒዎች፣ ኤሌክትሮኒክ ምስሎችና የማለፊያ ትኬት የሌላቸው ተንጠልጣ ባጆች ለመግቢያነት አያገለግሉም፡፡

**ጥ፡ የወረቀት ቫውቸርን ወይም ኢንር ኤጀንሲ ዓመታዊ የ4ኛ ክፍል ማለፊያ ትኬትን ጓደኛዬ እንዲጠቀምበት ማዋስ እችላለሁ?**
**መ፡** አይቻልም፡፡ እርስዎ፣ የማለፊያ ትኬቱ ባለቤት (የ4ኛ ክፍል ተማሪ) የማለፊያ ትኬቱ ጥቅም ላይ ሲውል በአካል መገኘት አለብዎ፡፡ ለሌላ ሰው ሊተላለፍ አይችልም፡፡